የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ.፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.19
ADDIS ABABA 30th March, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፯/፪ሺ.፲፬

ከሰም ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………………………..…………ገጽ ፲፬ሺ.፩፻፬

## Content

Regulation No. 497/2022

Kesem Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation …….…...............Page 14104

### ደንብ ቁጥር ፬፻፺፯/፪ሺ.፲፬

### ከሰም ስኳር ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “ከሰም ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፯/፪ሺ.፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. መቋቋም

፩/ ከሰም ስኳር ፋብሪካ ከዚህ በኋላ “ፋብሪካ” እየተባለ የሚጠራው፣ የፌደራል የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ከሰም ስኳር ፋብሪካ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

### REGULATION NO. 497/2022

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF KESEM SUGAR FACTORY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "Kesem Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 497/2022”.

2. **Establishment**

1/ Kesem Sugar Factory, hereinafter referred to as “The Factory”, is hereby established as a Federal Public Enterprise.

2/ Kesem Sugar Factory shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**፫.ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀፅ ፭፻፶ መሠረት የፋብሪካውን የንግድ ስራ ጉዳዮች የመምራት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የፋብሪካው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የከሰም ስኳር ፋብሪካ ዋና መስሪያ ቤት ዱሩፉሊ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ሥፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡

**፭. ዓላማ**

ፋብሪካው የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩/ የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ተክሎችን ማልማት፤

፪/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶች እና ተጓዳኝ ምርቶችን ማምረት፤

፫/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችንና ተጓዳኝ ምርቶችን በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኩል ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፬/ የፋብሪካውን የስኳር ልማት ማስፋፊያ መልሶ የማደስ ፕሮጀክቶችን ማቀድና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፭/ በአዋጪነትና በውጤታማነት ላይ ተመስርቶ እንደአስፈላጊነቱ ከአገዳ አብቃዮች ጋር ውል ገብቶ መስራት፤

፮/ ለፋብሪካው የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት መስራት፤

፯/ ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የሸንኮራ አገዳ እርሻ መሬት በሊዝ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ ማግኘትና በይዞታው ስር ማድረግና ማልማት፤

**3. Supervisory Authority**

Without prejudice to the right of the Ethiopian Sugar Industry Group Pursuant to Article 550 of the Ethiopian Commercial Code to direct the business affairs of the Factory, the Public Enterprises Holding and Administration shall be the supervising authority of the Factory.

**4. Head Office**

The head office of Kesem Sugar Factory shall be in Durufuli town and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

**5. Purpose**

The purposes for which Kesem Sugar Factory is established are:

1/ To grow sugarcane and other sugar yielding plants;

2/ To process and produce sugar, sugar by-products and co-products;

3/ To supply sugar and sugar by products and co-products to local as well as foreign market through the Ethiopian Sugar Industry Group;

4/ To plan sugar development expansion and overhaul projects within the factory and implement same upon approval;

5/ To work in agreement with sugarcane growers based on feasibility and effectiveness;

6/ Work to produce the required trained manpower in number, type and quality;

7/ Acquire use right on lease or by other legal means and develop agricultural land for sugarcane plantation;

፰/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫና የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል ተደራድሮ በመፈረም ገንዘብ መደበር፤

፱/ የፋብሪካውን የማምረት አቅም የሚጨምሩ አዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትን ሥልጠናንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር መደራደርና ውል መፈረም፤

፲/ በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ከሚከናወኑት በጋራ ማዕቀፍ ከሚገዙት ግዢዎች ውጪ ያሉትን የግዢ ውሎች በመዋዋል ግዢ መፈጸም፤

፲፩/ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮.ካፒታል

ለከሰም ስኳር ፋብሪካ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፲፱ ቢሊዮን ፩፻፷፰ ሚሊዮን ፴፮ ሺህ ፪ ብር ከ፶፪ ሳንቲም (አስራ ዘጠኝ ቢሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ስምንት ሚሊዮን ሰላሳ ስድስት ሺህ ሁለት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፬ ቢሊዮን ፯፻፺፪ ሚሊዮን ፱ ሺህ ብር ፷፫ ሳንቲም (አራት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ ሺህ ብር ከስልሳ ሶስት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፯. ኃላፊነት

ፋብሪካው ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

8/ In accordance with the policy direction and directives issued by the Ministry of Finance, Negotiate and sign loans with domestic as well as foreign financial institutions;

9/ Enter into a contract with other companies for introducing new technologies or training and other matters of importance that improve the factory's productivity;

10/ Execute procurements those are not included in the common procurement package that is carried out by The Ethiopian Sugar Industry Group;

11/ Engage in any other activity that is necessary to accomplish its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of Kesem Sugar Factory is Birr 19,168,036,002.52 (Nineteen Billion One Hundred Sixty Eight Million Thirty Six Thousand Two Birr and Fifty Two Cents) of which Birr 4,792,009,000.63 (Four Billion Seven Hundred Ninety Two Million Nine Thousand Birr and Sixty Three Cents) is paid up in cash and in kind.

## 7. Liability

The Factory shall not be held liable beyond its total assets

፰. **የቆይታ ጊዜ**

ከሰም ስኳር ፋብሪካ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

፱. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፬ዓ.ም**

**ዓብይ አህመድ(ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

8. **Duration**

Kesem Sugar Factory is established for an indefinite duration.

9. **Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this 30th Day of March, of 2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**